# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 197 የካቲት 15 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

በጉልበተኛ ወንበዴዎች በሚገዛ አገር ውስጥ የሃይማኖት ነፃነት ይኖራል ማለት ዘበት ነው። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሳይወገድ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥያቄ ምላሽ ያገኛል ብለን አናምንም።

የኢትዮጵያ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የጀመረው ትግል የሃይማኖት ጉዳይ ብቻ አይደለም። ትግሉ የነፃነት፣ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ጉዳይ ነው። እናም ሁላችንንን ያገባናል፤ በጋራ ቆመን ትግሉን እናፋፍም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጥምረትና ኦነግ በጋራ ያዘጋጁት የዋሽንግተን ዲሲ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱ ተገለጸ

በጄነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ከጥምረት ለነጻነት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ ጋር በመተባበር በአስራ አንድ ታላላቅ የሰሜን አሜሪካ፤ ካናዳና አውሮጳ ከተሞች ያዘጋጀው ህዝባዊ ስብሰባ ባለፈው ዕሁድ የካቲት 11፣ 2004 ዓ/ም በዋሽንግተን ዲስ ላይ መጀመሩ ታውቆአል።

በአገሪቱ ሰአት አቆጣጠር ከቀኑ 2pm ጀምሮ አለከሳንደሪያ ቨርጂኒያ በሚገኘው ሽራተን ሆቴል በተካሄደው የጥምረትና የኦነግ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ አዳራሹን ሞልቶ የተረፈ ብዛት ያለው ህዝብ የተገኘ መሆኑ ሲዘገብ የዕለቱ ተናጋሪዎች የተሰበሰበውን ህዝብ የሚያረካ ውይይት ማካሄዳቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል።

ጥምረትን በመወከል ንግግር ያደረጉት ሊቀመንበሩ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሲሆኑ የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በመወከል የተናገሩት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የውጪ ግንኙነት ሃላፊው አቶ ቃሲም አባነሻ ናቸው። አርቲስት ታማኝ በየነም የህብረት ትግል አስፈላግነትን አስመልክቶ ተወያዮችን ያስደሰተ ንግግር ማድረጉን ለማወቅ ተችሎአል።

## ኢትዮጵያዊያን አስተዳደጋችን፣ አኗኗራችንና አሰራራችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን አይሆንም ሲል የወያኔ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ጁነዲን ሳዶ አስትወቀ

ሚኒስትሩ ኢትዮጵያዊያንን በዚህ መልክ የገለጸው "የዜጎች ቻርተር "በሚል ከእንግሊዝ ቀዳነው ያለውን አዲስ የአሰራር ስርአት ማሻሻያ ሰነድ ለማስተዋወቅ በግዮን ሆቴል ገለጻ ባደረገበት ወቅት ነው።

ወያኔና ሆድ አደር ካድሬዎቹ ለኢትዮጵያዊን ያላቸውን ግልጽ ንቀትና ጥላቻ የሚያንጸባርቅ ነበር የወያኔው ሚኒስትር ገለጻ። ኢትዮጵያን ለ21 ኛው ክፍለ ዘመን አይሆኑም የሚል። እንደሚታወቀው ከተወሰነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ማንኛውም ፍጥረት ዕጣው መጥፋት ነው። እናም የጁነዲን አባባል ኢትዮጵያዊያን መጥፋት ያለባችሁ ፍጥረቶች ናችሁ የሚል አንድ ምታ ያለው ነው የሚሉት አንድአንድ አስተያየት ሰጪዎች ለመሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለዚህ ዘመን የማንመጥን ከሆነ ይህ "የዜጎች ቻርተር" የተዘጋጀው ለማነው ሲሉ ይጠይቃሉ? አያይዘውም ለዚህ የማንመጥነው ተራ ዜጎች ነን ወይስ ዲሞክራሲ፤ ፍትህና እኩልነት የምድራችን ፋሽን በሆነበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን በአራዊቴ ህግ አገር የሚያስተዳድሩ፤ የፖለቲካ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው ገና በመካከለኛው ዘመን ውስጥ ያሉ ኋላ ቀር የወያኔ ገዢዎችንም ይመለከታል ሲሉ ይጠይቃሉ።

ጁነዲን እንዳለው ቀደም ሲል በርካታ ገንዘብ ፈሶበት፣የትየሌሌ ጊዜ ባክኖበትና ሰፊ የሰው ሀይል ተሳትፎበት ለሀገሪቱ ስር የሰደደ የአሰራር ስርዓት ችግር መድህን ይሆናል ተብሎ የተጠናው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ለመከፋፈል ባደረገው ሴራ ሀይለኛ ግጭት ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ፍርሀት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር በገፍ አድስ አበባ እየገባ መሆኑ ተዘገበ

ህዝብን እርስ በርሱ እንዳይተማመንና እንዲከፋፈል በማድረግ የግፍ አገዛዝ ዘመኑን ከሁለት አሥርት አመታት በላይ በህዝብ ጫንቃ ላይ ጭኖ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የሙስሊሙን ህብረተሰብ በአክራሪነትና በለዘብተኝነት በመፈረጅ በቀሰቀሰው ክፍፍል ከፍተኛ ተቃውሞ እየገጠመው መምጣቱን ለማወቅ ተችሎአል። በዚሁ መሠረት ላለፉት 8 ሳምንታት ዘወትር አርብ በሙቶ ሺ የሚቆጠሩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በአወልያ መስጊድ በመሰባሰብ በነጻነት የማምለክ መብታቸው እንዲከበርላቸው፣ የሀይማኖት መሪዎቻቸውን በዲሞክራሲያዊ ሁኔታ እራሳቸው እንዲመርጡ እና አገዛዙ ጣልቃ እንዳይገባባቸው በመጠየቅ ላይ ናቸው።

የአገዛዙ በሃይማኖታቸው ጉዳይ ጣልቃገብነት እንዲቆምና ወያኔ ያለህዝብ ፈቃድ የሾማቸው መጂሊሶች እንዲባረሩ የሚጠይቁት በየሳምንቱ በአወሊያመስጊድ የሚሰበሰቡ ሙስሊሞች ጥያቄያቸውን ለአገዛዙ የሚያቀርቡ 17 ተወካዮችን መርጠው እንደላኩና ውጤቱን ለመስማት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የኦሮሚያ አርሶ አደሮች በመሬት ነጣቂዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመሩ፤ የፓኪስታን ኩባንያ ንብረት የሆነውን የሸንኮራ አገዳ ማሳ በእሳት አጋዩ

ኢትጵያዊያን ገበሬዎች ቤተሰቦቻቸውን መመገብ ተቸግረው እያለ ለፓኪስታን ሃብታሞች ለም መሬት በብላሽ የሚሰጥ መሆኑን ኢትዮጵያዊን ገበሬዎችን በእጅጉ አስቆጥቷል። ለውጭ አገር ሃብታሞች ሲባል በጂማና በምሥራቅ ወለጋ ዞኖች መካከል ከበደሌ ከተማ ወደ ነቀምት ከተማ በሚወስደው ደዴሳ ሸለቆ የሚገኘው መሬት አካባቢ 100 ሺሕ የሚጠጉ አርሶ አደሮች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ አርሶ አደሮች ከይዞታቸው እንዲነሱ ታዘዋል። እንቢ ሲሉም ጦር እየተላከባቸው ለሰቆቃ ተዳርገዋል። በዚህ የወያኔ ተግባር የተከፉ አርሶ አደሮች በፓኪስታኑ ኩባንያ የሸንኮራ አገዳ ማሳ ላይ እሳት ለቀውበታል። እሳቱንም ለማጥፋት ሁለት ቀናት ያክል መውሰዱም ተዘግቧል።

የፓኪስታኑ ኩባንያ አል ሐበሻ ስኳር ፋብሪካ ከሦስት ዓመታት በፊት በአካባቢው 26 ሺሕ ሔክታር መሬት በመረከብ የሸንኮራ አገዳ ልማት በማካሄድ ላይ ሲሆን ኩባንያው ከተረከበው ቦታ በተጨማሪ 26 ሺሕ ሔክታር መሬት ለማስፋፊያ ይፈልጋል።

ይህ በዚህ እንዳለ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ይፋ ባደረገዉ ዜና፤ በጋምቤላ ክልል አነድ የክልሉ የልዩ ኃይል ወታደራዊ አመራር መኮንንና አንድ የፖሊስ አባል መገደላቸዉን እንዲሁም ንብረትነቱ የሼክ መሐመድ አላሙዲ የሆነ የሳዑዲ ስታር እርሻ ልማት ኩባንያ የፋይናንስ ኃላፊና ሾፌራቸው መቁሰላቸውን አስታወቀ። የተገደለዉ የጋመቤላ የልዩ ኃይል አዛዥ አባንግ አማው ኡቹዶ የሚባል ሲሆን ቀደም ሲል ከነዚሁ አማጺያን ጋር ሸፍቶ የነበረና በኋላ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የፍትህ ታጋዩን አንዱአለም አራጌን የደበደበው ቅጥረኛ ሌላኛው የግፍ እስረኛ ናትናኤል መኮንን ወደታሰረበት ክፍል እንደተዛወረ ተገለጸ

ህዝባዊ አመጽ በመቀስቀስ ከሥልጣን መንበሬ ያፈናቅሉኛል ብሎ የሰጋቸውን የሰላም ታጋዮች በሽብርተኝነት ክስ ቃሊቲ ያወረደው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የፖለቲካ እስረኞች ባሉባቸው የእስር ቤት ክፍሎች ውስጥ ቅጥረኛ ወንጀለኞችን አሰርጎ በማስገባት በሽብርተኝነት የፈጠራ ወንጀል ተከሶ እስር ቤት እየማቀቀ ያለውን የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አንዱአለም አራጌን ባለፈው ሳምንት ክፉኛ አንዳስደበደበ መዘገባችን ይታወሳል።

የወያኔ የደህንነት ሃላፊዎች አንዱአለም አራጌን ለማስደብደብ ሆን ብለው ያስገቡት ኢብሳ አስፋዉ በሚል ስም የሚጠራዉ ይህ ቅጥረኛ ግለሰብ አንዱአለም አራጌ ላይ ለፈጸመው ድብደባ ምንም አይነት ቅጣት ሳይጣልበት ሌላው የፖለቲካ እስረኛ ናትናኤል መኮንን ወደታሰረበት ክፍል ተዛውሮ ከርሱ አጠገብ መኝታ ቦታ እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሎአል። እንደ እሥር ቤት ምንጮቻችን ደብዳቢው ኢብሳ አስፋው አንዱአለምን ለመደብደብ 2500 ብር የተከፈለው ሲሆን ግለሰቡ እውነተኛ ስሙ በእስር ቤት እየተጠራበት ያለው ኢብሳ መሆኑ አጠራጣሪ እንደሆነ ታውቆአል።

አንዱአለም ድብደባ በተፈጸመበት ወቅት ትግሪኛ ተናጋሪ የሆኑ የእስር ቤቱ ሃላፊዎች ዘር እየጠቀሱ፣ "አለኝ የሚለው ደጋፊ መጥቶ ያትርፈው" በማለት ሲናገሩ መደመጣቸውንና ትግሪኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ሌሎች የእስር ቤቱ ጠባቂዎች በሁኔታው ሲናደዱ እንደነበር ምንጮች ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አንባገኑን መለስ ዜናዊ በመቃወም በለንደን ታላቅ ሰልፍ እንደሚካሄድ ታወቀ

መለስ ዜናዊን የመሰለ አምባገነን አሸባሪና ዘረኛ መሪ፤ የሰላምና የመረጋጋት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ለአለም ህዝብ እናሳያለን! በሚል መሪ መፈክር ስር በተጠራዉ ታላቅ የተቃዉሞ ሰልፍ ላይ፤ በለንደንና አካባቢዉ የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያዉያንና የሶማሊያ ተወላጆች እንደሚገኙ የሰልፉ አስተባባሪ ቡድን Network against Repression & Injustice in Ethiopia ገልጿል።

በሶማሊያ ጉዳይ የብሪታኒያ መንግስት ሐሙስ የካቲት 23 ቀን 2012 በጠራዉ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ለመገኘት የሚመጣው ዘረኛው መለስ ዜናዊ፤ ራበን ዳቦ ይሰጠን፣ ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፣ ብለው የጠየቁ ንጹሀን ዜጎችን፤ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችንና ነፃ ጋዜጠኞችን በሽብርተኛነት የሃሰት ክስ በእስር በማሰቃየት ላይ የሚገኝ፤ በከተማም ሆነ በገጠር ዜጎችን ከነባር ይዞታቸዉ በተለያየ ምክንያት በማፈናቀል አገሪቷን ለውጪ ባለሃብቶች በማቀራመት ተግባር ላይ የተሰማራና በአፍሪቃ ቀንድ በየወቅቱ ስር እየሰደደ ለሚሄደዉ የሰላም እጦት በግንባር ቀደምትነት ተጠያቂ የሆነ ግለሰብ በመሆኑ በስብሰባዉ ላይ ለመሳተፍ የሞራል ብቃት እንደሌለው አስተባባሪዎቹ ጠቅሰዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄዎች የሁላችንም ናቸው!!!!

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያነሷቸው ጥያቄዎች የመብት ጥያቄዎች ናቸው። “በሃይማኖታችን አትግቡብን ማለት” መብት ነው። “የማንፈልጋቸው የማኅበራችንን መሪዎች ሽረን የምንፈልጋቸውን እንምረጥ” ማለት መብት ነው። “በትምህርት ጉዳይ ጣልቃ አትግቡ” ማለት መብት ነው።

ሙስሊም ኢትዮጵያዊን ከላይ የተጠቀሱትን የመብት ጥያቄዎችን በማንሳታቸው ሰበብ እየተፈለገ እየታገቱ፤ ማስፈራሪያና ዛቻ እየደረሰባቸው፤ ከዚያም አልፎ እየታሰሩ ነው። ዜጎች የራሳቸውን እምነት ራሳቸው መምረጥ በመፈለጋቸው “አሸባሪ፣ አክራሪ፣ ቅጥረኛ” ሌላም ሌላም እየተባሉ ለሰቆቃ እየተዳረጉ ነው። በመረጥናቸው መሪዎች ብቻ እንመራ ማለትም በግንቦት 7 አባልነት የሚያስፈርጅና የሚያስከስስ ወንጀል ሆኗል።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ የሙስሊም ዜጎቻችን ጥያቄዎች የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄዎች ናቸው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምርጫው የሆነ እምነትን የመከተልና የማምለክ መብት አለው። የማምለክ መብት የሰብዓዊ መብቶች አካል ነው። ሰብዓዊ መብቶች ደግሞ መሸራረፍ የለባቸውም።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያንን በራሱ ካድሬዎች ለመሙላት እያደረገ ያለው ጥረት በቤተክርስትያኗና በምእመናኗ ላይ ያደረሰውና እያደረስ ያለው ችግር ቀላል አይደለም። ከፍተኛ የሃይማኖት መሪዎች በወያኔ የስለላ ዱርዬዎች የደረሰባቸውን የአካል ድብደባው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ዛሬ ደግሞ ይህ ዘረኛ አገዛዝ ፊቱን ወደ እስላም ሃይኖትና ሙስሊም ኀብረተሰብ አዙሯል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ሃይማኖት ሲመርጥልን ዝም ብለን ልንቀበል አይገባም። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መቃወማቸው ተገቢ ነው። እንዲያውም ይህ ጥያቄ የሙስሊም ኢትዮጵዊያን ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች የሆኑ ኢትዮጵያዊያንም ጥያቄ ነው።

የሙስሊም መብት ተደፍሮ የክርስቲያኑ፤ የክርስቲያኑ መብት ተደፍሮ የሙስሊሙ ሊከበር አይችልም፤ አይገባምም። መብቶች ሃይማኖት የላቸውም። ስለሆነም ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጎን መቆም ለነፃነትና ዲሞክራሲ ግድ ያላቸው ዜጎች ሁሉ ኃላፊነት ነው።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይ ከሚያደርገው ጣልቃ ገብነት እጁን እንዲያነሳ ከመጠየቅ በተጨማሪ: -

1ኛ. በወያኔ የተጠለፈው የኢትዮጵያ እስላማዊ ምክር ቤት (መጅሊስ) እንዲፈርስና አዲስ ምርጫ እንዲደረግ፤ እና

2ኛ. አወሊያ የትምህርት ተቋም ከወያኔ ተጽዕኖ ነፃ እንዲሰራ

ያቀረባቸው ጥያቄ ተገቢና መሠረታዊ ናቸው ብለን እናምናለን። እነዚህ ጥያቄዎች የሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ጥያቄዎች ናቸው።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ አገራችንን አንድም ነፃ ተቋም የሌላት አድርጓታል። በአሁኑ ሰዓት ወያኔ የማይቆጣጠረው አንድም የሃይማኖት፣ ህዝባዊ፣ የልማትም ሆነ ማኅበራዊ ተቋም የለም። ነፃ ተቋማት በሌሉበት ነፃ አገር የለም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለተቋሞቻቸው ነፃነት የሚያደርጉት ተጋድሎ የሁላችንም ተጋድሎ ነው። በዚህም ምክንያት የሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ትግል መደገፍ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም የትግሉ አካል መሆን ይኖርብናል ብለን እናምናለን።

በጉልበተኛ ወንበዴዎች በሚገዛ አገር ውስጥ የሃይማኖት ነፃነት ይኖራል ማለት ዘበት ነው። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሳይወገድ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጥያቄ ምላሽ ያገኛል ብለን አናምንም።

ስለሆነም የትግሉ ስትራቴጂያዊ ግብ የመለስን አምባገነን ሥርዓት በማስወገድ በምትኩ ለሃይማኖቶች እኩልነት የቆመ መንግሥት መመሥረት ነው ብለን እናምናለን። ይህ ደግሞ የግንቦት 7 ንቅናቄ ዓላማ ነው። የግንቦት 7 ሙስሊም አባላት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በጀመሩት ትግል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። የሌሎችም ሃይማኖት ተከታዮች የሙስሊሙን ጥያቄ በሚመቻቸው መንገዶች ሁሉ መደገፍ ይኖርባቸዋል። በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ለእኩልነት፣ ለነፃነትና ዲሞክራሲ ግድ ያላችሁ የሙስሊም ማኅበረሰብ አባላትም ግንቦት 7ን እንድትቀላቀሉ ጥሪ እናደርጋለን።

የኢትዮጵያ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የጀመረው ትግል የሃይማኖት ጉዳይ ብቻ አይደለም። ትግሉ የነፃነት፣ የሰብዓዊ መብት እና የእኩልነት ጉዳይ ነው። እናም ሁላችንንን ያገባናል፤ በጋራ ቆመን ትግሉን እናፋፍም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ኢትዮጵያዊያን አስተዳደጋችን፣ አኗኗራችንና አሰራራችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን አይሆንም ሲል የወያኔ ሲቪል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ጥናት ግቡን አልመታም። ምክንያቱ ደግሞ የሰራተኛው በአመለካከት አለመለወጥ ነው። ይሁንና የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ውድቀት ትክክለኛ ምክንያት የወያኔ የጥናት አላማውን መጥምዘዝና ጌትነቱን ተቀብለው በሎሌነት ለማደር አሻፈረኝ ያሉ ሰራተኞችን ለመምቻ መገልገያ ማድረጉ መሆኑን የሚገልጹት ሰራተኞች በትግበራው ወቅት ብዙ ጠንካራ ሰራተኞች ከስራ ተባረው በምትካቸው ከየመስሪያቤቱ ሙያ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ካድሬዎች መመደባቸው የቅርብ ጌዜ ትዝታ ነው ብለዋል። እነኚሁ አስተያየት ሰጪዎች ዛሬም የሰራተኛው አመለካከት አለመለወጥ በምክንያትነት መነሳቱ እንደተለመደው ለሎሌነት እጅ አንሰጥም ያሉ ሰራተኞችን በካድሬ ለመተካት የተሰላ ቀሺም ሂሳብ ሊሆን እንደሚችል ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ወያኔ በተለያየ ጊዜ ለስርዓቱ በባርነት አናድርም ያሉ ባለሙያዎችን ለማሸበር ብሎም ከስራ ለማባረር የተለያዩ የማሻሻያ ጥናቶችን ሲጠቀምባቸው ቆይቷል። ከነኚህም ውስጥ የመዋቅር ማሻሻያ፣ ውጤት ተኮርና የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ የአሁኑ "የዜጎች ቻርተር" የሚለው የማሻሻያ ጥናት ከቀደምቶቹ በምን እንደሚለይ አይታወቅም።

---

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ለመከፋፈል ባደረገው ሴራ ሀይለኛ ግጭት ሊቀሰቀስ ይችላል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለየካቲት 26 ቀን 2004 ዓም ቀጠሮ እንደተሰጣቸው ባለፈው አርብ በመስጊዱ ተሰብስቦ ለነበረው ቁጥሩ ከ150 ሺ በላይ ለሚሆን ምዕመናን ገልጠው እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፉት ሁለት ቀናት ውስጥ "እንቅስቃሴያችንን ወደሌላ አቅጣጫ ለማዞርና ጥያቄያችንን ለመደፍጠጥ መጅሊስና በፌደራል ጉዳዮች ስር የሚገኘው የደህንነት ክፍል ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው" የሚል ወረቀት ተጽፎ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በስፋት እየተበተነ በመሆኑ በሙስሊሞች መካከል ደም አፋሳሽ የሆነ ግጭት ሊቀሰቀስ ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት መፈጠሩን የደረሱን ዘገባዎች ያመለክታሉ። በዚህም ምክንያት ወያኔ ብዛት ያላቸውን ወታደሮች ወደ ከተማው በገፍ እያስገባ መሆኑን የሚናገሩት ምንጮች ሆን ተብሎ በመንግሥት የተቀነባበረውን ይህን ችግር በሰላምና በድርድር ከመፍታት ይልቅ ወታደራዊ መፍትሄ ፍለጋ ወታደሮቹን በገፍ ወደ ከተማ ማስገባት የሚፈይደው ነገር እንደሌሌ ይገልጻሉ።

ኢሳት አስተማማኝ ያላቸውን ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው የወያኔ የፌደራል መንግስት የደህንነት መስሪያ ቤት በተቻለው መጠን ተቃራኒ ቡድን በመፍጠር ሽኩቻው በህዝብና በህገወጦቹ የመጅሊስ አመራር አባላት መካከል መሆኑ ቀርቶ በሁለቱ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው በሱፊያና በወሀብያ ሙስሊሞች መካከል እንዲሆን እየሰራ ነው ሲል አጋልጦአል።

---

## የኦሮሚያ አርሶ አደሮች በመሬት ነጣቂዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመሩ፤ የፓኪስታን ኩባንያ ንብረት የሆነውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ግን ወገኖቹን ከድቶ እጁን በመስጠት የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝን የተቀላቀለ የአኙዋክ ብሔረሰብ አባል እንደነበር ንቅናቄዉ ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ የዘገበ ሲሆን ግድያውንም የፈጸሙት የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ ወያኔ በአኙዋክ ንጹሃን ወገኖቻችን ላይ የፈጸመው የዘር ማጥፋት አስቆጥቷቸው የሸፈቱ አማጺያን እንደሆኑ ተገምቷል ብሏል።

የክልሉን ተወላጆች ከመሬታቸዉ በሀይል በማፈናቀል ለአረብ ለህንዶችና እንዲሁም ለወያኔ አባላቱ በመሸንሸን ያካባቢዉን ማህበረሰብ እያማረሩ ባሉ የወያኔ ባለሟሎች ላይ እርምጃ መዉሰድ መጀመራቸዉን ስንዘግብ መቆየታችን ይታወሳል። ይህ ምሬት ወደ ቁጣ ተለዉጦ ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ በዚሁ የጋምቤላ ክልል የመሳሪያ ግምጃ ቤት መዘረፉንና እንዲሁም በቅርቡ የክልሉ የወያኔ የምስጢር ደኅንነት ሹም የነበረዉ ጌታቸዉ አንኩሬ ቤቱ በር ላይ በጥየት ተደብድቦ መገደሉም መዘገባችን ይታወሳል፡፡

## የእሳት እራት
## ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር

*የምድር ፈራጅ ሆይ ከፍ ከፍ በል፤*
*ለትዕቢተኞች ፍዳቸውን ከፈላቸው።*

*አቤቱ ህዝብህን አዋረዱ፤*
*ርስትህንም አስቸገሩ።* *መዝሙረ ዳዊት 93/4 ቁ 2-5*

በ1993 ዓ.ም በካርታ ሥራ ድርጅት አዳራሽ ውስጥ ትልቅ ስብሰባ ይካሄዳል ተብሎ ውጭ ጉዳይ ሥራ በዝቶበት ሰንብቷል። አምባሳደሮች ከያሉበት በአስቸኳይ እንዲመጡ በተላከላቸው ደብዳቤ መሰረት ገስግሰው አዲስ አበባ ከተዋል። ወጪያቸው በሙሉ በመሥሪያ ቤቱ ይሸፈናል ስለተባለም ለእንቁጣጣሽ አዲስ ልብስ የተገዛለት ህጻን የሚፈነድቀውን ያህል በደስታ ተሳክረዋል። በዋንው መሥሪያ ቤት ውስጥም ከሶስተኛ ጸሃፊ በላይ ያሉ ብቻ በስብሰባው እንዲሳተፍ ማስተወቂያ በመለጠፉ ቀሪዎቹ የእንጀራ ልጅን ስሜት ተላብሰው በትዝብት ይመለከቱ ነበር።

አምባሰደሮቹም አንገታቸውን በካራባት አስረው ለንጉስ ሰርግ የተጠሩ እድምተኞችን መስለውና ከጣሪያ በላይ እየተሳሳቁ በተራ በተራ ወደ አዳራሹ እየገቡ ፊት ለፊት ከተደረደሩ ወንበሮች ላይ ይኮለኮላሉ። ከዚያም ግማሹ እየተሳለቀ፤ ቀሪው እየተሳተፈ ፤ሌላውም እያሳተፈ ስብሰባው ለድፍን አስራ አምስት ቀናት ተካሄደ።

የመጨረሻውን ቀን ስብሰባ መለስ ዜናዊ ስለሚመራው ተሰብሳቢው በሙሉ እርሱ ወደአለበት ተጠራ። እርሱ ህዝብ ወደአለበት መመጣትን ባለመፍቀዱ ብዙሃኑ ወደ እርሱ በሰልፍ ሄደ። ስዩም መስፍንም ከዚያ አለ። አንዴ ምንስቴር ዴእታ ሌላ ግዜ ደግሞ አምባሳደር ሲሉት ሁሉንም ይሁን ብሎ ተቀብሎ ባስቀመጡት የሚገኝ የቤቱ ጌጣ ጌጥ ተቀዳ ዓለሙም ከዚያ አለ።

መለስ ያለማቋረጥ ሲናገር ስዩም መስፍን በግንባሩ ወደ ቁልቁል የሚንዥቀዥቀውን ላብ ጠረጴዛ ላይ ባስቀመጣት መሃረብ መልሶ መላልሶ እየጠረገ ሳይታክት ይጽፋል። ከመለስ አንደበት ይሄ ነው የሚባል በጎ ነገር አይወጣም ስዩም ግን አንዷንም ቃል አይገድፍም። ተጀምሮ እስኪፈጸም ኮስተር ብሎ ይጽፋል። ደቂቃን ሠራተኞች በመለስ ንግግር ሳይሆን በስዩም መስፍን እንዲያ ሳይታክት መጻፍ በእጅጉ ተገረሙ። ምን የሚጻፍ በጎ ነገር አግኝቶ ይሆን በማለት ብዙዎች መገረማቸውን ተናግረዋል።

መለስ እንዲህ አለ “እናንተ አገሪቷን እያከሰራችሁ ነው። ዲፕሎማሲያችን ኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲ ነው። በነገራችን ላይ “ኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲ” የሚሉት ልመናን ነው። ኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲያችንን አልሠራችሁም። ማምጣት የሚገባችሁን “ሃርድ ካሽ” አላመጣችሁም። በዓመት 240ሚሊዮን ብር በጀት እየበላችሁ ምንም “ሃርድ ካሽ “አላመጣችሁም። ዋና ስራችሁ “ሃርድ ካሽ” ማምጣት ነው ሌላ ምንም ስራ የላችሁም። ዝም ብሎ ባንዲራ ማውለብለብ ምንም ዋጋ የለውም። በእናንተ ምክንያት ከስረናል ብሎ አምባሳደሮቹ ላይ አፈጠጠ። ”እንዲህ ሳያቋርጥ ሲናገር ስዩም መስፍንም ሳያቋርጥ ይጽፋል።

አንድ አምባሳደር እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ “የኢኮኖሚው ዲፕሎማሲ ያልተሳካልን ምናልባት ፖለቲካው ላይ አተኩረን ይሆን ?” ሲል ፈራ ተባ እያለ ጠየቀ።

መለስ ለአምባሳደሩ ጥያቄ እንዲህ ሲል መለሰ ”እናንተ ፖለቲካውን ሰርታችሁት አይደለም እስከ ዛሬ ይህች አገር የቆየችው። ከእናንተ በላይ የዚህችን አገር ፖለቲካ የሚሰሩልን አሉ። እርሱን በተመለከተ የምንፈልገውን ነገር በተሻለ ፍጥነትና በተሻለ የጥራት ደረጃ እዚህ ካሉ ከየአገራቱ አምባሳደሮች እናገኛለን። ”

ሌላም ጥያቄ ተከተለ ለምሳሌ ጋና ካለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ምን ዓይነት “ሃርድ ካሽ ማግኘት እንችላለን። እዚያ ያለው እምባሲ ባንዲራችንን እያወለበለበ ኢትዮጵያን ከማስተዋወቅ ውጪ ምን ሊሰራ ይችላል?”

መለስ ዜናዊ ነፍሱ በተቃርኖ የተሞላች ነች። ዛሬን እስካደረ ድረስ ለነገ የሚል ደግ አስተሳሰብ ያለው ጤነኛ ሰው አይደለም። እናም ስለ “ሃርድ ካሽ” ያወራውን በተመለከተ የተጠየቀውን ጥያቄ እንዲህ ሲል መለሰ “እኛ እያልን ያለነው ገንዘብ ሊሰጡ የሚችሉ አገራት ውስጥ የምትሰሩትን አምባሳደሮች ነው። ሃርድ ካሽ የማታመጡ ከሆነ ምን ልትሰሩ ነው ታዲያ ? ካሁን በኋላ ኪሳራውን ይዘን ለመቀጠል አንችልም” ብሎ አስፈራራ።
በዲፕሎማሲው መንደር ውለው የማያውቁ ካድሬዎችን አምባሳደር አድርጎ ሹሞ ሲያበቃ ይህን አልሰራችሁም ያን አላደረጋችሁም ብሎ መቆጣት ድንፋታ ይባላል። መለስ እንደልማዱ ደንፍቶ ደንፍቶ ሲያበቃ ስብሰባው ተፈጸመ ተባለ።

አንዱ አምባሳደር “እንግዲህ ሃርድ ካሽ ካልተገኘ የራሴን ደሞዝ አጠራቅሜ ይዤ እመጣለሁ” ብሎ ቀለደ ሲባል ሰምተናል። ይህ ግን ቀልድ አይደለም። ምሬት ነው።

በዚህ ስብሰባ ላይ እኔ አልተሳተፍኩም። ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብሮ ከመስራት ተሰድጀ ርቄ ብኖር ይሻለኛል ብሎ ቀየውን መንደሩን ጥሎ ወደ ሩቅ አገር የተሰደደው አለቃየ ከስብሰባው በኋላ ስንጫወት የነገረኝን መንደርደሪያ አድርጌ ወደ ራሴ ጉዳይ እዘልቃለሁ።

የራሴ ጉዳይ እንዲህ ይጀምራል፤

እግዜርን ፍራ። እግዜርን መፍራት ስታውቅ ሰው ትሆናለህ። ልጄ እባክህ ሰው ሁን እያለ ያሳደገኝ አባቴ አሁን በህይወት የለም። እግዜሩን ፈርቶ እኔንም እንድፈራ አድርጎ ኑሮ ሲያበቃ በቅርቡ አረፈ።

ማህበረ ሰቡም ገና ድሮ ህጻን ሳለሁ ፈሪሃ እግዚአብሄር ከሚገለጽባቸው ነገሮች መካከል አንዱ በአገር ላይ የተሾመን ሁሉ ማክበር ነው ብሎ አስተምሮኛል። መንግስቱ ኃ/ማሪያምን ያስነሳው አምላክ ነው። መለስ ዜናዊንም ያመጣው እርሱ ፈጣሪ ነው። እርሱ ያመጣውን እርሱ እስኪመልሰው ድረስ ጸጥ ለጥ ብለን ተገዝተን እንድንኖር ትእዛዝ እንዳለ እየተነገረኝ ለአቅመ አዳም ደረስኩ።

ታልቁ መጽሃፍም ትእዛዙን የሚጠራጠር አንዳች አያገኝም ብሎ አስፈራርቷል። የተሾመን ማክበር ለእርሱም መታዘዝ ፈጣሪን መፍራት እንደሆነ ከመቀበል ወጪ የተለየ እውቀት የሌላቸው ወላጆቼ ይሄን እውነት ነው ብለው ተቀብለውና መክረው አሳድገውኛል።

ሀ ሁ ብየ ፊደል ቆጥሬ አ ቡ ጊዳንም ዘልቄ የእውቀቴን ልቀትና ጥልቀት ላሳፋ አስቤ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ገባሁ። ከዚህ የዘላለም የሰው ልጆች ማደጊያ ሥፍራ ከፍ ባለ ማእረግ ተመረቅሁ። ከዩንቨርስቲ ካገኘሁት እውቀት ላይ የአቶ ሃዱሽ ገ/እግዚአብሄር መልካም ፈቃድ ታክሎበት በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ተቀጠርኩ። **ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል።**

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ያሉ ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጥን፣ የወረዳ መስተዳድሮችና ማዘጋጃ ቤቶች የህብረተሰቡን አመኔታ ያጡና የወረደ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው በሚል ተፈረጁ

የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዘገባ ተቋማቱን በዚህ ሁኔታ የፈረጀው "ሁለተኛው አገር አቀፍ የሙስና ቅኝት" በሚል ርእስ የስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ያስጠናው ጥናት መሆኑ ገልጾአል።

ህብረተሰቡ በፍትህ አካላትና መስተዳድሮች ይህን ያክል ተስፋ መቁረጥና አመኔታ ማጥቱ አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ምን ያህል በህዝብ ዘንድ እየተጠላ መምጣቱን የሚጠቁም ከመሆኑም ሌላ ህዝቡ በዘግናኝ የፍትህና የመልካም አስተዳደር እጦት እየተሰቃየ እንደሆነ የሚያመላክት ነው ተብሎአል።

የወያኔ ፍትህ አካላት አገዛዙን የሚቃወሙ ተቃዋሚዎችን፣ ሃያሲ ጋዜጠኞችን፣ የሰብዓዊመብት ተሟጋቾችን...ለመምታት በማጥቂያ መሳሪያነት ከማገልገል ባሻገር ለህብረተሰቡ የሚፈይዱት አንዳችም ፋይዳ እንደሌለ 6500 ግለሰቦችና ተቋማት ለጥናቱ በሞሉት መጠይቅ ገልጸዋል።

የተቋማቱ ጥቃት ሰለባ ነን ያሉ አንድአንድ ግለሰቦች በሙስና የተዘፈቁት ጉምሩክና ገቢዎች ባለስልጣን እንዲሁም የወረዳ መስተዳድሮችና ማዘጋጃ ቤቶች በህዝቡ ዘንድ የስቃይና የመከራ ማስፋፊያ ተቋማት በሚል እንደሚጠሩ ተናግረዋል። ከነዚህም ሌላ የኑሮ ውድነት፣ ስራ አጥነት፣ የትራንስፖርት ችግር፣ የመንገድ አውታር አለመስፋፋት፣ የምግብ እጥረትና ሙስና ስር የሰደዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በሚል በጥናቱ ተብራርተዋል።

ጥናቱ ላለፉት ስድስት ዓመታት ባለ ሁለት አህጎዝ እድገት እያስመዘገብኩ ነው እያለ ሲያደነቁረን የቆየው ወያኔ አመጣሁ የሚለው እድገት ከቁጥር ጨዋታ በመዝለል ለህዝቡ ችግር አንዳች ነገር ያልፈየደ አገዛዙ በምዕራባዊያን ለጋሾቹ ዘንድ በአገሪቱ ለውጥ ያመጣ መስሎ ለመታየት ለርካሽ የፖለቲካ ጠቀሜታ የሚነዛው ፕሮፖጋንዳ መሆኑን ያሳየ ከመሆኑም ሌላ ስለ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብት...እያለ የሚያነበንበው ሁሉ ከእውነታው በእጅጉ የራቀና ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ብቻ እንደሆነ ያረጋገጠ ነው ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች አብራርተዋል።

በአሁኑ ወቅት ህዝቡ ይህንን የስቃይና የመከራ ምንጭ የሆነውን ስርዓት ለማስወገድ በቃ ብሎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የሚናገሩት እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች የሰሞኑን የመምህራን የደሞዝ ጥያቄ፣የአወሊያ ት/ ቤት ንቅናቄ፣በጋምቤላ በመንግስት ባለስልጣናት ላይ እየተሰነዘሩ ያሉ ጥቃቶችን ለአብነት ጠቅሰዋል።

ይህን ጥናት ለማካሄድ ኪሊማንጃሮ ኢንተርናሺናል ኮርፖሬሺን የተባለ የታንዛኒያ ኩባንያ 468000 አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ የአሜሪካን ዶላር በዓለም ባንክ ተከፍሎታል።

## የወያኔ ተቋማት በህዝብ የተጠሉ መሆናቸውን የኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ሊሚትድ ጥናት አረጋገጠ

የዓለምባንክ፣ ኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ሊሚትድ የተሰኘ የታንዛኒያ ኩባንያን ቀጥሮ ባሠራው ጥናት ውጤት መሠረት (1) የዋጋ ንረት፣ (2) ድህነት፣ (3) ሥራ አጥነት፣ (4) የትራንስፖርት እጥረት፣ (5) የመንገድ አውታር ያለመስፋፋት፣ (6) የምግብ እጥረት፣ እና (7) ሙስና በኢትዮጵያ ስር የሰደዱ ማኅበራዊ ችግሮች መሆናቸውን አረጋገጠ።

ወያኔ ስለ ፈጣን እድገት በሚያወራበት በአሁኑ ሰዓትና ለሃያ ዓመታት ድህነትን እዋጋለሁ ካለ በኋላ ያመጣው ነገር ቢኖር የጥቂት ወያኔ አባላት መመንደግና የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወደ ባሰ ድህነት አዘቅት መወርወር መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል። ምንም እንኳን ጥናቱ የተደረገው ለወያኔ ቅርበት ባለው ድርጅት ቢሆንም ያፈጠጠውን እውነት መደበቅ አለመቻሉ የችግሩን ስፋት እንደሚያመለክት ጥናቱን የተመለከቱ ባለሙያዎች ገለጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በብዙ አገሮች የዋጋ ንረት፣ ድህነትና ሥራ አጥነት የመንግሥት ለውጥን የሚያስከትሉ ህዝባዊ አመጾችን የሚፈጥሩ በመሆኑ "የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በመርፌ ቢነኩት የሚፈነዳ ፊኛ ነው" የሚሉ ወገኞች ብዙ ናቸው።

ኢትዮጵያዊያን በወያኔዉ ተቋማት ላይ ያላቸውን አመኔታ በተመለከተም የኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ሊሚትድ ጥናት መጠነኛ ዳሰሳ ያደረገ ሲሆን በውጤቱም የወያኔ ፍርድ ቤቶች ከሁሉም በላይ የተናቁና የተዋረዱ ተቋማት መሆናቸውን ይፋ አድርጓል። እንደ ጥናቱ ውጤት ከወያኔ ፍርድ ቤቶች ፍትህ አገኛለሁ ብሎ የሚያምን የለም። ፍርድ ቤቶች ከማናቸውም በባሰ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ከፍርድ ቤት ቀጥሎ የህዝብን አመኔታ በማጣት ግንባር ቀደም የሆነው ተቋም ፓሊስ ሲሆን ከፓሊስ ቀጥሎ ደግሞ የጉምሩክና ገቢዎች ባለሥልጣን፣ የወረዳ መስተዳድር አካላትና ማዘጋጃ ቤቶች ይገኛሉ።

በአጠቃላይ ጥናቱ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በዘረኛ መንገድ የገነባቸው ተቋማት ምን ያህል በህዝብ የተጠሉ መሆናቸዉን ያመለክታል ተብሏል።

## ምርጫ ቦርድ ለአስር ፓርቲዎች ለማከፋፈል በሚል ከመንግስት ካዝና ወጪ ካደረገው 10 ሚሊዮን ብር ዉሰጥ 9 ሚሊዮን 989 ሺህውን ብር ወያኔ ለራሱ ወሰደው

ገንዘብ የማይጠረቃው ወያኔ 10 የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመደጎም በሚል ሰበብ 10 ሚሊዮን ብር በምርጫ ቦርድ አማካይነት ከባንክ ካስወጣ በኋላ ራሱ ወሰደው። ወያኔ ለዘረፋው የሰጠው ምክንያት ገንዘብ የምንከፋፈለው በ 2002ቱ ምርጫ ባሸነፍነው ወንበር ልክ ነው የሚል ነው። እንደሚታወቀው በ2002 ምርጫ ወያኔ "ኢህአዴግ" በተሰኘ የማስመሰያ ስሙ አማካይነት 99 ነጥብ 6 በመቶ አሸንፌያለሁ ማለቱ ይታወቃል።

ቦርዱ ወጪ ያደረገውን 10 ሚሊዮን ብር በምክር ቤቶች ወንበር ልክ እያሰላ የሚያከፋፍል ከሆነ፤ ከወያኔ ውጪ በምክር ቤት ውስጥ ወንበር ያለው ፓርቲ እንደሌለ እየታወቀ ገንዘቡ ለ10 ፓርቲዎች ይከፋፈላል መባሉ "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" እንዲሉ ነው ይላሉ ታዛቢዎች።

ጉዳዩን የተከታተሉ ታዛቢዎች እንደተናገሩት ከሁሉም የሚያስቀው ወያኔ ገንዘቡን በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ እንዲያስችለው የገንዘብ ክፍፍሉ በወያኔ ምክር ቤት ውስጥ ተመራጮች ባላቸው መቀመጫ ነው በሚል ሰበብ የአንድ የምክር ቤት ወንበር ዋጋ መሰላቱ ነው። በስሌቱ መሰረት የአንድ ምክር ቤት ወንበር ድርሻ 3 ሺህ 598 ብር ነው። በዚህም መሰረት ከ 10 ሚሊዮኑ ውስጥ ወያኔ በኢህአዴግ ስም ከ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ፤ አጋሮቼ ናቸው በሚላቸው ተለጣፊዎቹ ስም ደግሞ ከ 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በላይ በድምሩ እራሱን የ9 ሚሊዮን 989 ሺህ ብር ባለድርሻ አድርጓል።

ከወያኔና አጋሮቹ የተረፈችው 10ሺህ 794 ብር ወይም 0 ነጥብ 001 ፐርሰንቷ ስትሆን ይህቺው ገንዘብ ለሶስት የተቃዋሚ ፓርቲዎች መከፋፈሏ ተገልጾአል። የ10 ሺው ብር ቅርጫ የደረሳቸው መድረክ፣ መኢአድ እና በአየለ ጫሚሶ የሚመራው ቅንጅት ናቸው። ይህም የሆነው መድረክ በፓርላማ አንድ ወንበር ስላለው ሲሆን፤ መኢአድ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ባለው አንድ መቀመጫ እና በአየለ ጫሚሶ የሚመራው ቅንጅት በአዲስ አበባ ምክር ቤት ባለው አንድ ቦታ፤ እያንዳንዳቸው የአንድ ወንበር ዋጋ 3 ሺህ 598 ብር ወይም በወቅቱ ምንዛሬ 156 ዩሮ ደርሷቸዋል።

ይህ ገንዘብ ለፓርቲዎቹ ጽህፈት ቤቶች የአንድ ወር ኪራይ እንኳ አይሸፍንም። ንዘቡን ፓርቲዎቹ ለጽህፈት ቤት ሥራ ሊያውሉት ቢፈልጉ፤ አሁን ባለው የገበያ ዋጋ 20 እሽግ የደስታ ወረቀት ሊገዙበት ይችላሉ።

መድረክ የደረሰውን ገንዘብ ይቀበል፤አይቀበል እስካሁን ማረጋገጥ አልተቻለም። ገንዘቡን መቀበሉን የገለፀው መኢአድም፤ ለመመለስ መወሰኑን አስታውቋል።

ወያኔ ለገንዘብ ሲል የማይፈለቅለው ድንጋይ የሌለ መሆኑ ይህ ራሱ አንድ ምስክር ነው ይላሉ ታዛቢዎች።

## በሰሜን ጎንደር በደባርቅ ወረዳ የሥራ ማቆም አድማ አስተባብረዋል የተባሉ 40 መምህራን ከሥራቸው ታገዱ

በሰሜን ጎንደር ዞን በደባርቅ ወረዳ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ባለፈው ሳምንት የስራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውን ተከትሎ በተፈጠረ ውዝግብ ከ40 በላይ መምህራን ይቅርታ ካልጠየቃችሁ ስራ አትጀምሩም መባላቸውንና መምህራኑ ግን አሻፈረኝ ማለታቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ተሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ የተቃውሞ ሰልፉን ያስተባበሩት መምህራን የወረዳው መስተዳድር ያቀረበውን የይቅርታ ጥያቄ አንቀበልም በማለት በራሳቸው ጊዜ ማስተማር ቢጀምሩም፣ የወረዳው ባለስልጣናት ግን መምህራኑ እንዳያስተምሩ አግደዋቸዋል።

ይቅርታ ካልጠየቃችሁ ሥራ አትጀምሩም ከተባሉት መምህራን አንዱ ለኢሳት እንደተናገሩት የጠየቅነው የደሞዝ ይጨመርልን ጥያቄ ነው፣ ይህን ጥያቄ መጠየቅ ደግሞ መብት ነው፣ የስራ ማቆም አድማ ማድረግም ህገመንግስታዊ ሆኖ ሳለ የወረዳው ባለስልጣናት ግን ይቅርታ ካልጠየቃችሁ ስራ አትጀምሩም ብለዋል እኛም ይቅርታ አንጠይቅም፣ ብለን ተፋጠናል ማለታቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

በወያኔ የወረዳው ሹማምንት እምነት የታገዱት መምህራን ለሌሎቹ መጥፎ አርአያ በመሆናቸው ዳግም እንዳይለመዳቸው ይቅርታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል የተባሉ ቢሆኑም መምህራኑ ግን ጥያቄው የመላው ኢትዮጵያ መምህራን ጥያቄ እንጅ የደባርቅ መምህራን ብቻ አለመሆኑን በድፍረት እየገለጹ ነው ተብሎአል።

የአማራ ክልል መምህራን ያቀረቡት የደመወዝ ጭማሪና ሌሎች ተዛማጅ የመብት ጥያቄዎች በመላው የአገሪቱ መምህራን የሚደገፍ መሆኑን የሚናገሩ ምንጮች፤ ወያኔ ለመምህራኑ ጥያቄ አስቸኳይ ምላሽ ካልሰጠ ከትግራይ ክልል መምህራን ጋር በመተባበር ሊወስዱ ስለሚችሉት እርምጃ እየተወያዩ መሆኑን ይገልጻሉ። በመምህራኑ እርምጃ እየተደናገጡ ያሉት የወያኔ የክልል ተላላኪ ባለሥልጣናት መምህራኑ እንዲከፋፈሉና አንድ አቋም እንዳይይዙ ተግተው እየሰሩ መሆኑን ኢሳት ምንጮቹን ጠቅሶ ገልጾአል።

አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር እንዲዳከም ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ፣ መምህራን መብቶቻቸውን ማስከበር ተስኖአቸው ቆይቷል።

## የፍትህ ታጋዩን አንዱአለም አራጌን የደበደበው ቅጥረኛ ሌላኛው የግፍ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በእስር ቤቱ በተፈጸመበት ድብደባ ህክምና የተነፈገው አንዱአለም አሁንም ቢሆን ጭንቅላቱ ላይ የማያቋርጥ ህመም እየተሰማው እንደሆነ የገለጹት ምንጮቻችን ሆኖም በመንፈሱ ጠንካራ እንደሆነ አረጋግጠዋል።

ኢሳት በትናንትናው ዕለት ዘገባው እንደገለጸው የወያኔ ደህንነት ሆን ብሎ ያሰረገው ወንጀለኛ ማጅራት መቺ ሌላው የአንድነት አመራር አባል ናትናኤል መኮንን ወደታሰረበት ክፍል እንዲዛወር መደረጉ በርሱም ላይ ተመሳሳይ ድብደባ ለመፈጸም እንደሆነ ስጋት እንዳላቸው የድርጅቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ነጋሶ ግዳዳ መግለጻቸውን ይፋ አድርጎአል።

ዶር ነጋሶ ስጋታቸውን ወያኔ ለይስሙላ ላቋቋመው የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሃለፊ ለሆነው ለጥሩነህ ዜና በደብዳቤ መግለጻቸውን ሆኖም እስካሁን ድረስ ምንም መልስ እንዳላገኙም ኢሳት ዘግቦአል።

## ዘረኛውና አንባገኑን መለስ ዜናዊ በመቃወም በለንደን ታላቅ ሰልፍ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊ ለአገሪቱ ዜጎች መብትም ሆነ ለአካባቢው ደንታ የሌለው፤ የአሸባሪና ዘረኛ አገዛዝ ቁንጮ መሆኑን በጉባኤዉ ላይ ለሚሳተፉትና ለመላዉ አለም አቀፍ ህብረተሰብ እንደሚያሳዩ አስተባባሪዎቹ በበተኗቸዉ በራሪ ወረቀቶች አስታዉቀዋል።

ዘረኛው መለስ ዜንዊ ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚኖሩበት የምዕራባዊያን አገሮች ደርሶ ታላቅ ተቃውሞ ሳይገጥመው ተመልሶ እንደማያውቅ የታወቀ ሲሆን ከሁለት አመት በፊት ሎንዶንን በጎበኘበት ወቅት የተጋበዘበት ስብሰባ አዳራሽ ለመግባት እንደተቸገረና የሎንዶን ፖሊሲ በድበቅ በጓሮ በር አስገብቶ እንዳስወጣው መዘገቡ ይታወሳል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org